## Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)

766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010
Telephone: (202) 541-0556. FAX: (202) 541-0557
www.kinijitna.org


# የቅንጅትን መርሆዎች በሥራ የመተርጎም ኃላፊነት

የሀገራችን ታሪክ በርካታ የጦርነትና የደም መፋሰስ ምዕራፎችን ያዘለ ነው። ችግሮችን በኃይልና በነፍጥ የመፍታት ጎጂ ባህል ቁጥሩ በውል የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን ሕይወት በኢትዮጵያውያን እጅ እንዲያልፍ ምክንያት ሆኗል።

የቅንጅት እንቅስቃሴ ልዩነቶችን በጠመንጃ የመፍታት ባህል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ማስወገድ ላይ ያተኮረ ነው። የቅንጅት ራእይ...

> *"የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ሙሉ በሙሉ የተከበሩባት ኢትዮጵያን፣ ለሕዝቡ ፍላጎት መሟላት በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰራ አመራር፣ በሁሉም ደረጃ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት የሚሰራ መልካም አስተዳደር፣ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት ያለውና ራሱን ከኋላ ቀርነትና ድህነት ለማውጣት አብሮ የሚሰራ ሕዝብ ማየት ነው።"*

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ከቅንጅት ኋላ የተሰለፉት ቅንጅት ይዟቸው በተነሳው መርሆዎችና እሴቶች ልባቸው ስለተነካ ነው። በከተማም በገጠርም የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅንጅትን ሲመርጥ እነዚህ በማኒፌስቶው ውስጥ የተካተቱ መርሆዎች ተስማምተውኛል ብሎ ነው። በዚህ ረገድ የቅንጅት ማኒፌስቶ በቅንጅትና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የተደረገውን የቃል ኪዳን ውል የሚገልጽ ነው ማለት ይቻላል። በሰነዱ ውስጥ ከተዘረዘሩት 16 እሴቶችና መርሆዎች መሃከል ቅንጅት በሰላማዊ ትግል የሚያምን እንደሆነ የሚገልጸው ይገኝበታል።

> *"ቅንጅት ምንም ያህል መሰዋዕትነት ቢያስከትልም ለሰላማዊ ትግል ይሰለፋል። በአግባቡ የተያዘና የሚመራ ሰላማዊ የሕዝብ ትግል፣ እንደ እኛ በብዙ አሰጨናቂ ሁኔታ የተከበበን ሕብረተሰብ፣ ወደተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግር ተዓምር ይፈጥራል ብሎ ያምናል።"*

ይላል ማኒፌስቶዉ። ቅንጅት ለሰላማዊ ትግል ብቻ እንደሚሰለፍ፤ ሰላማዊዉ ትግል መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል፤ ሰላማዊዉ ትግል ለዉጥን እንደሚያመጣና ተዓምር እንደሚፈጥር፤ ሰላማዊ ትግል የዓላማ ጽናትንና የሰከነ አመራርን እንደሚጠይቅ በግልጽ ተስቀምጧል።

በማኒፌስቶው መሠረት ሰላማዊ ትግሉን ማጠናከር አማራጭ የማይገኝለት መንገድ ነዉ። ገዢዉ ፓርቲ እያደረሰ ያለዉ ኢሰብዓዊ ግፍ የማንፈልገውን የትግል አማራጭ እንድናሰላስል የሚያደርግ ሁኔታ ለፈጥር እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነዉ። ሆኖም ግን ኢትዮጵያውያን እንደገና ደም መፋሰስ አዙሪት ውስጥ ላለመግባት በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት በካርዳቸው አማካይነት ተናግረዋልና የሰላማዊ ትግሉን ጎን ስልታዊ በሆነ መንገድ እያጎለበትን ከመጓዝ በስተቀር ሌላውን አማራጭ ማስተናገድ አንችልም። የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር አባላት በሚገኙባቸው ከተሞች እንዲሁም ማሕበሩ በሚያካሂዳቸው ኮንፈራንሶች አማካይነት በዚህና በተመሳሳይ ርዕሶች ላይ ጠቃሚ ውይይቶች እይተካሄዱ ናቸው።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር ሃገር ዉስጥና በዉጭ የሚደረገዉ ሕዝባዊና ሰላማዊ ትግል ገዢዉ ፓርቲ የሕዝብን ጥያቄ እንዲሰማ የማስደረግ ችሎታ አለው ብሎ ያምናል።

ሜይ 12 እና 13 2007 ዓ/ም የሚካሄደው የማሕበራችን ጠቅላላ ጉባዔ እስካሁን በተግባር ያዋልነው ስልት የሰጠንን ተመክሮና ደካማ ጎን የማገናዘብና የዲሞክራሲ ትግሉ የበልጥ ውጤታማ በሆነ ጎዳና እንዲጓዝ አማራጮችን የማጤን አደራ ተጥሎበታል። በዚህ ረገድ ሕብረተሰቡ በድጋፍ ቻፕተሮቹ ፕሮግራሞች ውስጥ ይብልጥ በመሳተፍና ለሚቀርብለት ጥሪ ምላሺ በመስጠት የበኩሉን እንዲወጣ አደራ ጭምር እናሳስባለን።

የቅንጅት ሰላማዊ መንገድ ብቸኛው መንገድ ነዉ!
ኢትዮጵያ በአንድነቷና በነጻነቷ ለዘላለም ተክብራ ትኖራለች!
ሜይ 2 ቀን 2007 ዓ/ም